# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 317 ግንቦት 29 2006

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የወያኔ ፋሺስታዊ የጥፋት ፕሮጀክት እየተናደ ነው። በተስፋና በወኔ የተሞሉ ከሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተውጣጡ ወጣቶች በበረሃዎችና በሜዳዎች ላይ በአንድነት ሲዘምሩ ስናይ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ቅርብ መሆኑ ይሰማናል። አዎ!!! የኢትዮጵያ ወጣቶች ከየአቅጣጫው እየመጡ ነው። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ህልማቸውን ያልማል፤ ዜማቸውን ያዜማል። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ሁሌም አብሯቸው ነው። ኢትዮጵያ በወጣቶቿ ብርቱ ትግል ከአገዛዝ ነፃ ትወጣለች።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በመላው ሀገሪቱ ውጥረት እንደነገሰ ተጠቆመ

ሕወሃት መራሹ ወያኔ በሁሉም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንደገባ ተጠቆመ። የሚቀጥለውን ዓመት ሀገራዊ ምርጫ በዚህም በዚያም ብሎ አጭበርብሮና ሰርቆ አሸንፍኩ ለማለት ይረዳው ዘንድ፤ በሁሉም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች እየተዘዋወረ በሚያደርገው ልማት አምጥተናል አይነት ዲስኩር ብዙም ያልተደሰቱ ወገኖች፤ ወቅታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከሕወሃት አፋጣኝ መልስ እንደሚፈልጉ በማሳወቃቸው ያልጠበቀው ችግር ውስጥ እንደገባ እየተገለጸ ይገኛል።

በመላ ኦሮሚያ ተፈጥሮ የነበረውን ችግር እንፈታለን ከሕዝብም እንነጋገራለን በሚል ሰበብ በያቅጣጫው ሕዝብን በመሰብሰብ ለማነጋገር የሞከረው የሕወሃቱ ጀሌ ኦህዴድ በሀገሪችን እንደፈለግን መንቀሳቀስ አልቻልንም፣ ልጆቻችን በሰላም ወጥተው መመለስ አልቻሉም፣ የኑሮ ውድነቱ ካቅም በላይ ሆኗል፣ የመኖሪያ ቤት እጥረት መናገር ከሚገባን በላይ ከመሆኑም ባሻገር ይባስ ብሎ ያለ በቂ ካሳ እና ማስጠንቀቂያ በላያችን ላይ እንዲፈርስ ይደረጋል፣ መልካም አስተዳደር የሚባል ነገር የለም በዚህ የተነሳም አንድን ትንሽ ጉዳይ ለማስፈጸም ያለ የሌለ ሃብታችንን በእጅ መንሻነት መገበር ይኖርብናልና ሌሎችንም በመጠየቅ ሕወሃትን ጭንቅ ውስጥ እንደከተቱት ተጠቁሟል።

ሕዝብን አነጋግራለው ብሎ የዘመተው የሕወሃቱ ጀሌ ኦሕዴድም እፈታዋለሁ ያለውን ስር የሰደደ ችግር ለመፍታት ይቅርና መድረክ ላይ የቀረቡለትን ጥያቄዎች መመለስ ተስኖት ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ብቻ ስብሰባዎችን ልሳኑ በሆነው ራዲዮና ቲቪ ሲለፍ እንደከረመ የሚታወስ ሲሆን የአድስ አበባ አዲስ ማስተር ፕላን የቀሰቀሰው ችግር ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ዘረኛዉ ወያኔ አለም አቀፍ ነጻ ሜዲያዎችን የማፈን ክስ ሊመሰረትበት ነዉ

ሰሞኑን ጋዜጠኞችንና ጦማሪዎችን ሰብስቦ ወህኒ በመጨመር ቀድሞም በወረቀት ላይ በቀር በተግባር ያልነበረውን የመናገርና የመጻፍ ነጻነት ጨርሶ ማፈኑ ሳያንሰው ፋሽስት ወያኔ በተለያዩ አቅጣጫዎች የሌሎችን ዜና ማሰራጫ ጣቢያዎች በማፈን ክስ ሊመሰረትበት እንደሆነ ተጠቆመ።

ሰሞኑን በወጡት አዳዲስ የክስ ሪፖርቶች መሰረት መሰረቱን በእንግሊዝ ያደረገውና ቢቢሲ በመባል የሚታወቀው የዜና ማሰራጫ ተቋም የስርጭት መርሃግብሩን ከማፈን እንዲቀጠብ ፋሽስት ወያኔን ያስጠነቀቀ ሲሆን በተለይም በምስራቅና ሰሜን አፍሪካ እንዲሁም በመካከለኛው ምስራቅ የሚያደርገውን የአገልግሎት ስርጭት ከማፈን እንዲቆጠብ የህወሃት ባለስልጣናት የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ሲል ማስጠንቀቁ ተሰማ። የአፈና ተግባሩ ባጋጣሚ ሳይሆን ሆን ተብሎና በጥናት እየተከናወነ ነው ያለው ቢቢሲ እንዲህ አይነቱ ተግባር ዴሞክራሲን እየገነባን ነው በማለት በሰፊው ከሚያወራ ቡድን የሚጠበቅ አይደለም ሲልም አማሯል። እንዲህ አይነቱ ስራችንን የሚያበላሽ ተቀባይነት የሌለው ተግባር ባፋጣኝ መቆም አለበት ያለው የቢቢሲ ክስ ከቢቢሲ ጋር እንደ ዶቼ ቬሌ፣ ፍራንስ 24 እና ቪኦኤን የመሳሰሉ ዜና ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ህወሓት በዉኃ ስም ለጅቡቲ መሬት ቁርሶ ለመስጠት የስምምነት ፊርማ ማኖሩ ታወቀ

በፋሽስቱ ወያኔና በጂቡቲ መንግሥት መካከል የተፈረመውና የውኃ አቅርቦት ስምምነት የሚል ሽፋን የተሰጠው ህገወጥ የመሬት ችሮታ ለማፅደቅ ለጉጅሌው ወያኔ ፓርላማ የቀረበው ረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ ሰነድ እንደሚያሳየው ኢትዮጵያ በሺኒሌ ዞን ለውኃ ማሠራጫ 20 ሔክታር መሬት ለጅቡቲ የሰጠች መሆኗን በመግለጽ የውኃ ልማቱ ለሚካሄድበት ደግሞ 4 ሺሕ ሔክታር መሬት በተጨማሪነት ለመስጠት መስማማቷን ያመለክታል።

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ አካሄድኩት የሚለው ጥናት እንዳመለከተው በኢትዮ ጂቡቲ ድንበር 100 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው *በሺኒሌ ዞን በኩሊ ሸለቆ* የውኃ ክምችት መኖሩ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## በወያኔ መሪዎች ትዕዛዝ በየቦታዉ የሚረሸኑ ንፁሃን ዜጎች ጉዳይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደረሰ

የነፍሰ በላው ህወሓት ቡድን በኢትዮጵያውያን ላይ የሚያደርሰው አደገኛ የሆነ ዘረኝነትን ያዘለ የጥላቻ መከፋፈል እና ንፁሃን ዜጎችን ለማጥፋት የሚያደርገው ሩጫ እየተጋለጠበት እንደሚገኝ ምንጮቻችን ያደረሱን መረጃዎች ያመለክታሉ። በተለይ በመላ አገሪቱ በፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ሚሊሻዎች የሚረሸኑ ንፁሃን ዜጎች መበራከት አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ ታውቋል።

እንደ ምንጮቻችን ዘገባ በቅርቡ በሰሜን ሸዋ በተለምዶ አለባቸው ጫካ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ውስጥ የነፍሰ በላው ሕወሓት ቅጥረኞች 6 የኦሮሞ ተወላጆችን እንደረሸኑዋቸው የታወቀ ሲሆን ከረሸኑዋቸው በኋላ በጅምላ እንደቀበሩዋቸው ለማወቅ ተችሏል። አለባቸው ጫካ እየተባለ የሚጠራው አካባቢ ከነፍሰ በላው ወያኔ እስር ቤቶች እና የማሰቃያ ቦታዎች አንዱ ሲሆን በቦታው በፋሽስቱ ወያኔ ትዕዛዝ በርካታ ንፁሃን ዜጎች እንደተረሸኑበትና አሁንም በከፍተኛ ጥበቃ ብዛት ያላቸው ዜጎች ታጉረው የሞት ቀናቸውን እየተጠባበቁ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል።

በትግራይ ክልል በራያ ዓዘቦ ወረዳ ካለፈው ወር ጀምሮ 25 ሰላማዊ ሰዎች ወያኔ ቅጥረኛ ታጣቂዎች መገደላቸው ታውቋል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የደብረ ዘይት ነዋሪዎች ብሄራቸውንና ሃይማኖታቸውን እንዲያስመዘግቡ ተገደዱ

ዜጎችን እንደ ሰብዐዊ ፍጡር በእኩልነት በአንድ አይን ሳይሆን በዘር፤ በቋንቋን በጎሳ ከፍፍሎ የሚመለከተዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ባስተላለፈዉ መመሪያ መሰረት የደብረ ዘይት ከተማ ነዋሪዎች ዘራቸዉንና ሀይማኖታዉን የሚጠይቅ ቅጽ በመሙላት ላይ መሆናቸዉን ከከተማ የሚደርሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ። የተለያዩ የደብረ ዘይት ከተማ ነዋሪዎች በስልክ ደዉለዉ እንደነገሩን ፖሊሶች ከሲቪል ሰራተኞች ጋር በመሆን ቤት ለቤት እየዞሩ የነዋሪዎችን ብሄር እና ሃይማኖት ሲመዘግቡ ውለዋል። እንዲህ አይነቱ የዜጎችን ብሄርና ሃይማኖት ማንነት የሚጠይቅ ቅጽ መሙላቱ ለዜጎችም ሆነ ለአገሪቱ ምን እንደሚጠቅም ባይታወቅም ነገሮችን በዘር መነጽር ብቻ ለሚመለከተዉ ወያኔ ግን እንዲህ አይነቱ መረጃ የሚያጠቃቸዉንና አገልግሎት የሚከለክላቸዉን ሰዎች ለመለየት እንደሚጠቀመዉ ለማወቅ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ ከሌሎች አገሮች ልምድ እንደምንረዳዉ ዜጎችን በዘር ለይቶ መመዝገብና ማወቅ ህበረተሰብን እርስ በርስ ከማጨራረስ ዉጭ ሌላ ፈይዳ እንደሌለዉ በግልጽ የታየ ጉዳይ ነዉ።

"የምዝገባው አላማ ሰዎችን እየመረጡ ለማፈናቀል ሊሆን ይችላል" በማለት ስጋታቸውን የገለጹት ነዋሪዎች፣ብሄርን መመዝገቡ ለምን እንዳስፈለገ ሲጠይቁ ከላይ የተላለፈ መመሪያ ነው በሚል እንደተነገራቸው ገልጸዋል። አንዳንድ አስተያየት የጠየቅናቸው ነዋሪዎች በበኩላቸው ምዝገባው ከመጪው ምርጫ ጋር የተያያዘ ሳይሆን እንደማይቀር አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። በክልሉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታየ ያለው አለመረጋጋት እና በገዢው ፓርቲ እንደተቀነባበረ የሚታመኑ አልፎ አልፎ የሚነሱ አካባቢን ማእከል ያደረጉ ግጭቶች በቀበሌው ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ተጨማሪ የስጋት ምንጭ ሆኗል።

## ወያኔ መረጃ የሚያዘቡ 235 የድረ ፕሮፓጋንዲስቶችን ሁለት ዙር አሰልጥኖ አስመረቀ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን ህዝብ የመረጃ ጨለማ ዉስጥ ከትቶ የሚያሰቃየዉ አልበቃ ብሎት በየድገጹና በተለያዩ ማህበራዊ ሜዲያዎች ላይ እየገቡ ህዝብ የሚለዋወጠዉን መረጃ ማዛባትና ህዝብ ከህዝብ ጋር መረጃ እንዳይለዋወጥ ማድረግ የሚሞክሩ 235 የድረገጽ ሽፍቶችን አሰልጥኖ በስራ ላይ ማሰማራቱ ተሰማ። የወያኔ አገዛዝ ከአገር ዉስጥና ከዉጭ አገሮች በሜዲያ በተለይ በኢንተርኔት ሜዲያ እየደረሰበት ያለውን ትችት ለመቀነስና ፤ አገዛዙ ከህዝብ የተደበቁ ናቸዉ የሚላቸዉን መረጃዎች ለመቆጣጠር በማሰብ ከተለያዩ አካባቢዎች ሰብስቦ ያሰለጠናቸዉን ወጣቶች ተቃውሚዉን ጎራ የማዳከም ወይኔያዊ አደራ ሰጥቷቸዉ ከሰሞኑ ስራ እንዲጀምሩ አድርጓል። ከዉስጥ አዋቂ ምንጮች በደረሰን መረጃ መሰረት የእነዚህ ስልጡኖች ተቀዳሚ አላማ ፌስ ቡክ፤ ቲዉተርና ብሎጎችን በራሳቸዉ ስም በመክፈት ተቃዋሚ እየመሰሉ የዲሞክራሲ ኃይሎች የሚያደርጉትን የመረጃ ልዉዉጥ ማዛባትና በዜጎች መካከል አለመተማመን እንዲፈጠር ማድረግ ነዉ። አዲስ አበባ ዉስጥ ከሚገኙና ለአገዛዙ ቅርብ ከሆኑ ምንጮች ባገኘነዉ መረጃ መሰረት እነዚህ የሳይበር ሽፍቶች እስካሁን ድረስ 2 ሺ 350 የፌስ ቡክ፤ የብሎግ አካውንቶችን ከፍተዋል።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወጣቶች እየመጡ ነው!!!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ "ወጣት፤ የነብር ጣት!" በሚል ርዕስ ጥር 26 ቀን 2003 ዓ.ም. በቁጥር 142 ባወጣው ርዕሰ አንቀጹ "ወጣት በነብር ጣት መመሰል ያንሰው እንደሆን እንጂ አይበዛበትም። የኢትዮጵያም ወጣት የነብር ጣት ሆኖ ያውቃል ... አሁንም ነው" ብሎ ነበር። በዚያ ጽሁፍ እና በሌሎችም አጋጣሚዎች በተደጋጋሚ እንዳብራራው ግንቦት 7 በወጣቱ ችሎታና ተነሳሽነት ላይ ከፍተኛ እምነት አለው። የወደፊቷ ብቻ ሳይሆን የአሁኗ ኢትዮጵያም የወጣቱ መሆኗን ግንቦት 7 ያምናል። ግንቦት 7: ወጣቶችን ለማሳተፍና ለመሪነት ለማብቃት የሚጥር፤ ራሱም በወጣቶች የተገነባ ድርጅት ነው።

ኢትዮጵያ አገራችንና ሕዝቧን ከወያኔ አደንቋሪ አገዛዝ ለማላቀቅ ቆርጠው የተነሱ ወጣቶች እየበረከቱ መምጣታቸው የግንቦት 7 እምነትን የሚያጠናክር ሆኗል። አምባገነኑን የወያኔ አገዛዝን በትጥቅ ትግል መፋለም ይኖርብናል ብለው የተነሱ ወጣቶች በከፍተኛ ፍጥነት እየተደራጁ መሆናቸውን እንሰማለን። እድሜያቸው በሀያዎችና በሠላሳዎች መጀመሪያ ላይ የሚገኙ ለጋ ወጣቶች ናቸው የግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል የሚባለውን የትግል ድርጅትን የፈጠሩት። ይህ ኃይል ሰሞኑን ለአራተኛ ጊዜ እጩዎችን አሰልጥኖ ማስመረቁን በተለያዩ ሚዲያዎች ባሰራጨው ዜና ገልጿል። በተመሳሳይም የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶችን አሰልጥኖ ለወሳኝ ትግል ዝግጁ መሆኑን አብስሯል። የኢትዮጵያ አርበኖች ግንባርም በወጣቶች የተሞላ ለትግል የተዘጋጀ ድርጅት ነው። ሌሎችም አሉ። እነዚህን ድርጅቶች ድርጅት ያደረጓቸው ወጣቶች ናቸው።

በሰላማዊ የትግል ዘርፍም ወያኔ የሚያደርስባቸው እስር፣ ዱላና እንግልት እየተቋቋሙ በየእለቱ እየበረቱ የመጡ ጀግኖች ወጣቶችን ማየት ችለናል። ወያኔ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ብሩህ አዕምሮና ልብ ያላቸው ወጣቶችን አስሬ፣ አሸማቅቄ ጨረስኩ ሲል ከዚያ የባሱ እየፈለቁ ነው። በነፃነት ሲጽፉ የነበሩ እነ እስክንድር ነጋ፣ ውብሸት ታየ እና ርዕዮተ ዓለሙ በሀሰት ክስና ምስክር ሲታሰሩ ወያኔ ተስፋ እንዳደረገው ወጣቶች በፍርሃት ተሸማቀው ልሳኖቻቸውን አልዘጉም። እንዲያውም ከነሱ የባሱ፣ የበሰሉ ጦማርተኞች መጡ። ሰላማዊ ታጋዮቹ እነ አንዱ ዓለም አራጌና ናትናኤል መኮንንን ሲያስር ከእነሱ የበለጡ ወጣት ወንድና ሴት ታጋዮች መጡ። እስከ ድል ድረስ ይህ ዑደት ይቀጥላል፤ ኢትዮጵያ ወጣት ጀግኖችን ማፍራቷ አያቋርጥም።

ወያኔ "ኢህአዴግ" በሚባል ቀፎ በሰበሰባቸው አድርባይ ድርጅት ውስጥ የተሰባሰቡ ወጣቶችም ወደ ህሊናቸው እየተመለሱ፣ ድፍረት እያገኙና እየከዱት ነው። በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች በወያኔ ድርጅቶች ውስጥ የገቡ ህሊና ያላቸው ወጣቶች "ምን እናርግ?" እያሉ ነው። ለእነዚህ ወገኖቻችን ግንቦት 7 አጭር ምላሽ አለው - "ከቻላችሁ ጥላችሁ ውጡና የነፃነት ትግሉን በይፋ ተቀላቀሉ፤ ካልቻላችሁ ኢህአዴግን ከውስጥ ሆናችሁ ውጉት፣ አዳክሙት፣ ግደሉት"።

በሁሉም ረገድ በኢትዮጵያ ወጣት ላይ ያለ ተስፋን የሚያጠናክሩ ነገሮችን የምናስተውልበት ወቅት ላይ መሆናችን የሚያስደስት ነገር ነው። "እንዴት ልታገል? ከማን ጋር ልታገል?" የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል። ነፃነቱን የሚወድ ወጣት ሁሉ እንደ ፍላጎቱና ዝንባሌው የሚሳተፍበት መድረክ ተዘጋጅቶለታል።

ወያኔ፣ ወጣቱን ያህል የጎዳው የኢትዮጵያ የኅበረተሰብ ክፍል የለም። የህወሓት መሪዎች በወጣትነታቸው ዘመን "መብት ተነፈግን" ብለው ብረት አንስተዋል፤ የዛሬው ወጣት ግን እነሱ ያኔ የነበራቸውን እኩሌታ ያህል እንኳን መብት እንዳያገኝ አድርገዋል። የህወሓት ሁሉንም ጠቅልሎ የመግዛት ፍላጎት ወጣቱን መናገርም ሆነ መፃፍ ብቻ ሳይሆን ማሰብ እንኳን እንዳይችል ለማድረግ እየሞከረ ነው።

የኑሮ እድሎች የሚከፋፈሉት በዘርና በፓለቲካ ወገንተኝተኝነት በመሆኑ ከሁለቱም ያልሆነው ወጣት ኑሮው የተጎሳቆለ፤ የነገ ተስፋውም የጨለመ ሆኗል። ስደት የኢትዮጵያ ወጣት እጣ ፈንታ ሆኗል። ዛሬ የተማረውና ከተሜው ብቻ ሳይሆን በትምህርት ያልገፋውና በገጠር በግብርና የሚተዳደረውም ወጣት ስደተኛ ሆኗል። አረብ አገራት፣ ሱዳን፣ ኬኒያ፣ ደቡብ አፍሪቃ በኢትዮጵያውያን ወጣት ወንዶችና ሴቶች ተጨናንቀዋል። ወያኔ ወጣቱን በእድሜና በዝንባሌ ሳይሆን በዘር በማደራጀት የጎንደሩ ለባሌ፤ የሸዋው ለአሩሲ፤ የትግራዩ ለባህርዳር፣ የደሴው ለለቀምት ፈጽሞ ባዕድ እንዲሆን፤ በጥርጣሬም እንዲጠባበቅ፤ በሰበብ አስባቡም እንዲቆራቆስ አድርጓል። ወያኔ፣ የኢትዮጵያን ወጣት በኢትዮጵያ ወጣት ላይ እንዲዘምት አድርጓል።

ያም ሆኖ ግን የወያኔ ፋሺስታዊ የጥፋት ፕሮጀክት እየተናደ ነው። በተስፋና በወኔ የተሞሉ ከሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተውጣጡ ወጣቶች በበረሃዎችና በሜዳዎች ላይ በአንድነት ሲዘምሩ ስናይ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ቅርብ መሆኑ ይሰማናል። አዎ!!! የኢትዮጵያ ወጣቶች ከየአቅጣጫው እየመጡ ነው። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ህልማቸውን ያልማል፤ ዜማቸውን ያዜማል። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሁሌም አብሯቸው ነው። ኢትዮጵያ በወጣቶቿ ብርቱ ትግል ከአገዛዝ ነፃ ትወጣለች።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## በመላው ሀገሪቱ ውጥረት እንደነገሰ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ግን አሁንም ድረስ በመላ ኦሮሚያ ቁጥር አንድ ጥያቄ ሆኖ እንቅስቃሴ እየተደረገበትና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ከኦሮሚያ ሕዝብ ጋር በአንድ ላይ እንዲቆሙ ከፍተኛ ጥሪ እየተደረገበት እንደሆነ ተጠቁሟል። ይህን የተገነዘበው ሕወሃትም እንዲህ አይነቶቹ መተባበሮችና መተጋገዞች እንዳይኖሩ ለማድረግ በሌሎችም አካባቢዎች ተመሳሳይ ችግሮች እንዲነሱ ለማድረግ እየሞከረ መሆኑም ተያይዞ ተገልጿል።

በመሆኑም በክልል ሶስት ታላላቅ ከተሞች ከከተሞች መስፋፋት ጋር የተያያዙ የይዞታ ነጠቃና ቤቶች ማፍረስ አይነት ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ መናፈሱና በደብረ ማርቆስ ከተማ የከተማ መስፋት የጠቀለላቸው አርሶ አደሮች ህገወጥ ግንባታ ገንብታችኋል በሚል ቤቶቻቸው ያለምንም ማረጋገጫና ካሳ እየፈረሱ መሆናቸው በክልሉ ውጥረት እንዳነገሰ ተጠቁሟል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ለረዥም ጊዜ ሲብላላ የከረመው የወያኔ ጦር የደመወዝ ጭማሪና የስልጣን ማመጣጠን ጥያቄ ሰሞኑን ልክ እንደ አዲስ ፈንድቶ የሕወሃት ሌላ ጭንቅ እንደሆነ ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ጠቆሙ። ከታች ባለው የሰራዊቱ ክፍል እና ጥያቄውን መመለስ አለበት ተብሎ በሚጠበቀው የህወሃት ጥቂት ቁንጮዎች መካከል አለመግባባቱ ከፍተኛ እንደሆነ የሚጠቁሙት ምንጫችን፤ ይህ ጥያቄ በተለይ የአማራው ተወካይ በሚባለው ብአዴንና ሕወሃት መካከል የተካረረ ንትርክ ከማስነሳቱም በላይ የነበረውን ያለመተማመን ክፍተት ይበልጥ እንዳሰፋው ተጠቁሟል።

በትግራይ ከአረና ፓርቲ እንቅስቃሴና በክልሉ ሰፊ ተቀባይነት ማግኘቱን ተከትሎ ሕወሃት መራሹ ወያኔ የጅምላ እስርን ጨምሮ ይቃወማሉ የሚባሉትን የክልሉን ተወላጆች ወደ እስር እያጋዘ መሆኑም ተገልጿል። የምርጫ መሰረቴ ነው የሚለውን ትግራይን ሊያሳጣው እንደሚችል የገመተውን የአረና ፓርቲ አባላትን ማሰሩና ማዋከብ መጀመሩ ደግሞ በክልሉ በተለያዩ ወረዳዎች የሰላም መደፍረስና ከፍተኛ ውጥረት ፈጥሮ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ እየተዘገበ መሆኑም ተያይዞ ተገልጿል።

## ወያኔ መረጃ የሚያዛቡ 235 የድረ ፕሮፓጋንዲስቶችን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ኢህአዴግ በአዳማ ናዝሬት በሁለት ዙር ያሰለጠናቸው 235 ብሎገሮች በፌስ ቡክና በተለያዩ የማህበራዊ የመገናኛ መንገዶች፣ተቃዋሚ የሚመስሉ ስያሜዎችን በማውጣት ህዝብ የማደናገር፤ መንግስትን በሚቃወሙ መረጃዎች ላይ ምላሽ የመስጠት ፤ መንግስትን የሚደግፉ መረጃዎች በየጊዜው በመረጃ መረቡ ለህዝብ እንዲደርስ የማድረግ ተልእኮ ተሰጥቷዋል።ስልጠናውን የወሰዱት ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ የኢህአዴግ ደጋፊዎች ሲሆኑ፣ ምርጫውን ያካሄዱት የመንግስት ኮሚኒኬሽን እና የኢህአዴግ ሊግ ናቸው፡፡ ሰልጣኞቹ ተጠሪነታቸው በክልሉ ላሉ የኢህአዴግ መሪ ፓርቲዎች ሲሆን፣ የመንግስት ከሚኒኬሺን መስሪያቤት በበኩሉ መረጃዎችን በበላይነት የማረም እና የማስተካከል ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

በቅርቡ በተካሄደ የመጀመሪያው ዙር አፈፃፀም የአማራ ክልል መልካም ውጤት ማስመዝገቡን፤ በፌስቡክ አመራርነት ለቤነሻንጉል ጉሙዝ ተሞክሮ ማካፈሉ መደነቁን የመንግስት ኮሚኒኬሺን ሚኒስትር ሬድዋን ሁሴን በባህር ዳር ላይ በተካሄደው የመንግስት ከሚኒኬሺን ባለሙያዎች ግምገማ መናገራቸው ይታወሳል፡፡የኢህአዴግ የስልጠና መምሪያ ሃላፊ አቶ አዲሱ ለገሰ ደግሞ ከኢሳት ከሚወረወረው የጦር ፕሮፓጋንዳ መዳን የምንችለው በኢቲቪ ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ ሚዲያው ነው ሲሉ ለተመራቂዎች ተናግረዋል።

## እየራበንም ቢሆን በምግብ እራሳችንን ችለናል - ኃ/ማሪያም ደሳለኝ

ወያኔ ስልጣን በያዘባቸዉ አመታት በተለይም ባለፉት አስር አመታት የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ በድርብ አኃዝ አደገ፤ ኢትዮጵያ በ2015 ዓም መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች ተርታ ትሰለፋለች፤ በኤሌክትሪክ ኃይል እራሳችንን ችለን ለጎረቤት አገሮች እንተርፋለን፤ በቅርቡ ደግሞ በምግብ ምርት እራሳችንን ቻልን  የሚሉ በአይን የማይታዩና በእጅ የማይዳሰሱ የ"ላም አለኝ በሰማይ" ክምሮች እየከመረ የኢትዮጵያን ህዝብ ለመደለል ሞክሯል። የአገሩ ኤኮኖሚ በእጥፍ አደግ ሲባል ችግርና መከራዉ በሦስት እጥፍ የጨመረበት የኢትዮጵያ ህዝብ ግን እንኳን መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች ተርታ ሊሰለፍ ከሦስቱ ዕለታዊ ምግቦች አንዱን በቅጡ መብላት ተስኖት መብራት በሳምንት አንድ ቀን ብቻ እያገኘ "ጽድቁ ቀርቶብኝ በወጉ በኮነንከኝ" እያለ ጨለማ ቤት ዉስጥ ቁጭ ብሎ የመከራ ዘመን መቁጠር ጀምሯል።

የኢትዮጵያ ህዝብ እንመራሀለን ከሚሉት የወያኔ መሪዎች እጅ እጅ ብሎ የሰለቸዉ ነገር ቢኖር እንደሰዉ በእግሩ ቆሞ የሚሄደዉ ዉሸታቸዉና ቅጥፈታቸዉ ነዉ። የወያኔ መሪዎችና እዉነት አንድ ላይ ታይተዉ ስለማያዉቁ ህዝብ አይኑ እያየ የሆነዉን ነገር አልሆነም ወይም ጭራሽ ያልተሞከረዉን ነገር ሆነ ብለዉ ሲዋሹ ለአፋቸዉም ለሰብዕናቸዉም አይሳሱም። ለምሳሌ ሠላማዉ ዜጎችን በጅምላ ገድለዉ ብርድልብስ ጠቅልለዉ እየቀበሩ  ማንንም አልገደልንም፤  መብቱን የጠየቀ ሰላማዊ ሰልፈኛ በጥይት እየጨፈጨፉ - ባንክ ተዘረፈ፤ መሬታችንን ለምነዉ ለሱዳን እየሰጡ - የተሰጠ መሬት የለም፤ አኝዋክን ከመሬቱ አፈናቅለዉ መሬቱን ለባዕዳንና ለቤተሰቦቻቸዉ በርካሽ እየቸበቸቡ ኢትዮጵያ ዉስጥ የመሬት ቅርሚያ የለም እያሉ የዋሿቸዉ ግዙፍ  ዉሸቶች ከብዙዎቹ ቂቶቹ ናቸዉ።

ከአስራ ሰባት አመት የጫካ ዉስጥ ቆይታ በኋላ አዲስ አበባ የገቡት ዋና ዋናዎቹ ወያኔዎችም ሆኑ እነሱ መለምለዉ ያሰለጠኗቸዉ ምስለኔዎች የተካኑበት አንድ ትልቅ ነገር ቢኖር ዉሸት መደርደርና ከበስተኋላዉ ምንም ትርጉም የሌለዉ ቁጥር እየደመሩ  የኢትዮጵያን ህዝብና አለም አቀፉን ማህበረሰብ ማታለል ነዉ። አዎ! የወያኔ መሪዎች ከምንም ነገር በላይ ቁጥር ይወዳሉ። የሚናገሯቸዉ ቁጥሮች እነሱን የሚጠቅሙ ከሆነ ለጥጠዉ ለጥጠዉ ሰማይ ያደርሷቸዋል፤ የቁጥሮቹ ማነስ የሚጠቅማቸዉ መስሎ ከታያቸዉ ደግሞ ይጠቅሙናል ብለዉ ባሰቡት ልክ ያሳንሷቸዋል። ለምሳሌ አለም አቀፍ ዕርዳታ ሰጪ አገሮችና ተቋማት 6 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ተርቧልና አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ያስፈልገዋል ብለዉ ሲያስጠነቅቁ . . . . ወያኔ ደግሞ የለም የተራበዉ ህዝብ ከአንድ ሚሊዮን ያነሰ ነዉ ይላል። ለወያኔ ትልቁ ቁም ነገር የኢትዮጵያ ህዝብ የረሃብ አደጋ ላይ መዉደቁ ሳይሆን እራሱን ሞቶ ከተቀበረ ስርዐት ጋር ማወዳደርና የተሻለ መስሎ መቅረብ ብቻ ነዉ።

ወያኔ እንደሚናገረዉ እዉነትም የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ በድርብ አኃዝ አድጎ ቢሆንና በዚህ እድገት ዉስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ችግርና መከራ ያንን ያክል ተቀርፎ ቢሆን ኖሮ ወያኔን እንኳን መጣህልን ብሎ ከማመስገን በቀር አይንህን ላፈር ብሎ የሚቃወመዉ ቀርቶ አፉን ሞልቶ የሚያማዉም ዜጋ አይኖርም ነበር፡፡ ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ የመርገም ቀን ብሎ የሚጠራዉ ግንቦት ሃያም እንደዛሬዉ በግድ ሳይሆን እንደ የካቲት ሃያ ሦስትና እንደ ሚያዝያ ሃያ ሰባት የኢትዮጵያ ህዝብ በቀበሌ ተገድዶ ሳይሆን በራሱ ተነሳስቶ ደስ ብሎት የሚያከብረዉ በዐል ይሆን ነበር። ሀቁ ግን ወያኔ ኤኮኖሚዉ በድርብ አኃዝ አደገ በተባለ ቁጥር የኢትዮጵያ ህዝብ ችግርና መከራ በሦስት እጥፍ ያድጋል፤ የኤሌክትሪክ ኃይል አምርተን ለጎረቤት አገሮች ልንሸጥ ነዉ በተባለ ቁጥር ኢትዮጵያ ዉስጥ የመብራት አገልግሎት እንደ ምግብ ራሺን በሳምንት አንዴ ለዚያዉም ለተወሰኑ ሰዐታት ታይቶ የሚጠፋ የህልም እንጀራ ሆኗል።

አገራችን ኢትዮጵያ እንደ ፈረንጆቹ የዘመን አቆጣጠር በ2015 መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች ጎን ትሰለፋለች ተብሎ የተነገረንን የሞኞች ተስፋማ አንዱኑ አለመስማቱ ይሻለን ነበር። በ2102 ዓም በአለማችን ከፍተኛ ገቢ አላቸዉ ከተባሉት አገሮች ዉስጥ አንዷ ፖላንድ ነበረች፤ የፖላንድ ህዝብ በ2012 ዓም የነፍስ ወከፍ ገቢ $ 12660 በ2012 ሲሆን ፖላንድ ከፍተኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች የመጨረሻዋ ነበረች። በዚሁ በ2012 ዓም መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች አንዷ አልባኒያ ስትሆን በ2012 ዓም የአልባኒያ ህዝብ የነፍስ ወከፍ ገቢ $4030 ነበር፤ አልባኒያ መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች ዉስጥ የመጨረሻዋ ናት። በ2012 ዓም የኢትዮጵያ ህዝብ የነፍስ ወከፍ ገቢ $380 ነበር። ይህንን እጅግ በጣም ዝቅተኛ የሆነ ገቢ ነዉ "የማይነጋ መስሏት ምን እንዲሉ"  በ2015 ዓም $4000 ይደርሳል ብለዉ መለስ ዜናዊና ሱፊያን አህመድ የዛሬ አምስት አመት የነገሩን። ዛሬ የፈረንጆቹ 2015 ሊገባ የቀረዉ ስድስት ወር ብቻ ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ የነፍስ ወከፍ ገቢ እንኳን 4000 ዶላር ሊደርስ ለዘመናት ከሰነበተበት ደሃ ከሚባሉ አገሮች ጋርም ሲወዳደር ዝቅተኛ ከተባለበት ደረጃ እንደ ግመል ሽንት ወደ ኋላ እንጂ ወደፊት ሲራመድ አይታይም።

እስከ ሐምሌ 2004 ዓም ድረስ ከላይ በጠቀስናቸዉ የዉሸት ክምሮች ህዝብንና አገርን ሲያታልል የከረመዉ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ነበር። በእርግጥ መለስ ዜናዊ ላይመለስ ተሰናብቶን ሄዷል፤ ሆኖም እሱን ተካ የተባለዉ ሰዉ መለስ በአምሳያዉ የፈጠረዉ ሰዉ ስለሆነ ጌታዉ በአደራ መልክ ጥሎለት የሄደዉን ተልዕኮ በመፈጸም ላይ ይገኛል። ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ጥርስ የሌለዉን ስልጣን ተሸክሞ በሰራባቸዉ ባለፉት ሁለት አመታት ለሱዳን መንግስት ሽልማት ሆኖ በቀረበዉ መሬት ጉዳይ፤ በሰላማዊ ሰልፍ ጥያቄ፤ በዕድገትና ትራንስፎርሜሺን ጉዳይና በሌሎችም ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያደረጋቸዉ ንግግሮችና የሰጣቸዉ አስተያየቶች በሙሉ እንደ ካርቦን ኮፒ ከጌታዉ ከመለስ ዜናዊ የተቀዱ ንግግሮች ናቸዉ።  መለስ ዜናዊ ሞቶም ኢትዮጵያን እየገዛ ነዉ የሚባለዉ እንደነ ኃ/ማሪያም አይነቶቹን በቁማቸዉ የሞቱ ሰዎች ተክቶ ስለሄደ ነዉ።

ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በቅርቡ እሱን እራሱን ጨምሮ ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ ግዞት ዉስጥ የገባበትን ግንቦት ሃያ ቀንን የድልና የነጻነት ቀን ነዉ ብሎ ሲናገር ተደምጧል። ግንቦት ሃያ ኢትዮጵያ ዉስጥ የዘረኝነት፤ የጎጠኝነት፤ የሙሰኝነትና የአፈና መሰረት የተጣለበትን ቀን ነዉ፤ ኃ/ማሪያም ይህንን ቀን የኢትዮጵያ ዳግማዊ ትንሳኤ ቀን ነዉ ማለቱ የሚያሳየን ግለሰቡ ከኢትዮጵያና ከታሪኳ ጋር አለመተዋወቁንና እሱም የአገሩን የኢትዮጵያን ታሪክ የሚመለከተዉ እንደ ጌቶቹ በቁጥር ወስኖ መሆኑን ነዉ። ግንቦት ሃያ የኢትዮጵያ ህዝብ ሁለት እጆቹን በሰንሰለት አስሮ ከያዘዉ ስርዐት እጆቹና እግሮቹ ወደ ታሰሩበት ስርዐት የተዘዋወረበት ዳግማዊ የባርነት ቀን ነዉ። በእርግጥ ግንቦት 1983 ሰዉ በላዉ የደርግ ስርዐት የተደመሰሰበት ቀን ነዉ፤ ግን ግንቦት ሃያን የዳግም ነጻነት ቀን የሚያሰኘዉ የደርግ መደምሰስ ብቻ ሳይሆን ከደርግ መደምሰስ ጋር የኢትዮጵያ ህዝብ ከታሰረበት ሰንሰለት ተላቅቆ ቢሆን ነበር።  በተግባር የተመለከትነዉ ግን ግንቦት ሃያ የኢትዮጵያ ዳግማዊ ባርነት ቀን መሆኑን ነዉ።

ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በዚህ  ግንቦት ሃያ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ነዉ በሚለዉ አስጸያፊ ንግግሩ ብቻ አልተወሰነም . . .  እንደዚህም ብሎ ነበር። በሁለት አስርተ አመታት ዉስጥ 250 ሚሊዮን ኩንታል በማምረት በአገር አቀፍ ደረጃ በምግብ እራሳችንን ችለናል፤ በአለም ህብረተሰብ ዘንድ በረሃብና በድርቅ ትታወቅ የነበረቸዉ አገራችን በሁለት አስርተ አመታት ትግል በምግብ እራሳችንን ችለናል ብሎ በሙሉ አፉ ተናግሯል።

አገራችን ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ስትችል ተጠቃሚዎቹ ዝናብና ዳመና ፊታቸዉን ባዞሩብን ቁጥር የእርዳታ ለጋሾችን እጅ የሚመለከቱት ወገኖቻችን ናቸዉና አገራችን ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ቻለች ሲባል የማይደሰት ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለንም፤ የዛሬዉ ጉዳያችን ኢትዮጵያ እንዴት በአጭር ግዜ ዉስጥ በምግብ እራሷች ቻለች ሚለዉ ጥያቄ ጋር አይደለም። ኢትየጵያ ሰርቶ የሚያሰራና እንዲሁም እድገቷንና ብልጽግናዋን የሚመኝ መሪ አለመኖሩ ነዉ እንጂ ሃያ አመት እንኳን በምግብ እራስን ለመቻል ለሌሎችም ብዙ ነገሮች የሚበቃ ረጂም ግዜ ነዉ። የዛሬዉ ጥያቄያችን እዉነትም አገራችን ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ቻለች ወይ፤ ወይም ኢትዮጵያ ካሁን በኋላ የምግብ እርዳታ አያስፈልጋትም ወይ የሚል ነዉ። ለመሆኑ ኢትዮጵያ ዉስጥ በገሃድ የሚታየዉ እዉነታና የኃ/ማሪያም ደሳለኝ በምግብ እራሳችንን ችለናል ብሎ የተናገረዉ ንግግር አብረዉ ጎን ለጎን ይሄዳሉ?

መለስ ዜናዊ ከሃያ ሁለት አመታት በፊት የኢትዮጵያ ህዝብ በአጭር ግዜ ዉስጥ በቀን ሦስቴ የመብላት ዋስትናዉ ይረጋገጣል ብሎ ነበር። ዛሬ ከሃያ ሁለት አመታት በኋላ ከ40 በመቶ በላይ ኢትዮጵያዉያን እንኳን በቀን ሦስት ግዜ ምግብ ሊበሉ አንዱንም ጠግበዉ የሚበሉት የታደሉ ናቸዉ። መለስ ዜናዊን የተካዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የጌታዉን ትምህርት ተከትሎ ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ችላለች ብሎ ይናገር እንጂ እሱ እራሱ ከሚመራቸዉ ካቢኔዎች አንዱ ከሆነዉ ከግብርና ሚኒስቴር በቅርብ የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተዉ በ2006 በጀት አመት ብቻ 2.2 ሚሊዮን ኢትዮጵያዉያን ከፍተኛ የምግብ ችግር ዉስጥ እንደሚወድቁ ተናግሯል፤ ልብ በሉ ወያኔ እንደዚህ አይነቱን እሱን የሚያጋልጥ ቁጥር ማሳነስ እንጂ እዉነቱን መናገር አይወድም። ኢትዮጵያ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ እንደተናገረዉ እዉነትም በምግብ እራሷን ችላ ቢሆን ኖሮ በዉሸት ከተካነዉ የኃ/ማሪያም አፍ ይልቅ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ የእህል ገበያዎች በግልጽ በነገሩን ነበር።  ከኢትዮጵያ በየግዜዉ የሚወጡት የገበያ መረጃዎች ቁልጭ አድርገዉ የሚያሳዩን የምግብ ዋጋ በየቀኑ እያሻቀበ ሲሄድ ነዉ። የአገራችን የምግብ አቅርቦት በጨመረ ቁጥር ዋጋዉ ይቀንሳል እንጂ አይጨምርም ፤ወይም ሌላ ሁሉ ቢቀር የምግብ ምርት መጨመር ገበያዉን ያረጋጋዋል እንጂ የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ ኡኡ በሚያሰኝ መልኩ 2000 ብር አይደርስም ነበር።

በቅርቡ የአለም ባንክ፤ ለጋሽ አገሮችና የወያኔ አገዛዝ በጋራ ያወጡት ሰነድ በያዝነዉ አመት 2.7 ሚሊዮን ኢትዮጵያዉያን አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ካልተደረገላቸዉ ህይወታቸዉ አደጋ ላይ እንደሚወድቅ ይናገራል። ይህ የጋራ ሪፖርት ኢትዮጵያ እንደ ፈረንጆቹ ዘመን አቆጣጠር በ2013 ብዛት ያለዉ የምግብ ምርት አምርቻለሁ ብትልም የተመረተዉ 231ሚሊዮን ኩንታል አገሪቱን መቀለብ እንደማይችልና አገሪቱ በያዝነዉ የፈረንጆቹ አመት 388635 ሜትሪክ ቶን የምግብ ዕርዳታ እንደሚያስፈልጋት በግልጽ አስቀምጧል።ኃ/ማሪያም ደሳለኝ አስተምሮት ያለፈዉ ጌታዉ በቀን ሦስቴ እንበላለን ብሎ አንደዋሸን እሱም ረሃብ እየቆነደደን በምግብ እራሳችንን ችለናል ብሎ ቢዋሽ ብዙ አይገርመንም። ሆኖም አንድ የሚገርምም የሚያሳዝንም ነገር አለ፤ እሱም ኃ/ማሪያም በምግብ እራሳችንን ችለናል ብሎ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የዞንዘጠኝ ጦማርያን ተጨማሪጊዜተጠየቀባቸው

መረጃ ሰብስቦ ዜጎችን በመረጃ ላይ ተደግፎ ከማሰር ይልቅ መጀመሪያ ዜጎችን አስሮ ከዚያ ላሰረበት ምክንያት መረጃ ለመሰብሰብ የታሰሩ ዜጎችን ቤት እየሰበረ የሚገባዉ ፀረ ህዝቡ የወያኔ አገዛዝ በዞን ዘጠኝ ጦማሪያን ላይ በረጃ ለመሰብሰብ በሚል ሰበብ የሚያራዝመዉን ቀጠሮ አሁንም ስራዬ ብሎ እንደተያያዘዉ ከወያኔዉ ፍርድ ቤት የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። በተቀረዉ አለምም ሆነ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ሆን ብለዉ የፍርድ ቤት ቀጠሮዎችን ለእሁድ ቀን እየያዙ አንዴ ችሎቱ አልተሟላም አንዴ አቃቤ ህጉ አልመጣም እያሉ ተከታታይ ተጨማሪ የ28 ቀናት ቀጠሮ በመጠየቅ የታሳሪዎችን መብት ማስከበር የሚገባዉ ፍርድ ቤት ጭራሽ በተቃራኒዉ የእስረኞችን መብት በመርፈጥ ላይ ነዉ። በያዝነዉ ሳምንት መጀመሪያ ላይ ተጨማሪ የ28 ቀናት ቀጠሮ የተጠየቀባቸው የዞን 9 ጦማርያን ማህሌት ፋንታሁን፣አቤል ዋበላና በፍቃዱ ኃይሉ ናቸው።

ጦማርያኑ የዛሬ አስራ አምስት ቀን ፍርድ ቤት ቀርበው ፖሊስ ተጨማሪ የ28 ቀን ቀጠሮ ሲጠይቅባቸው በመሀል ዳኛዋ ውድቅ ተደርጎ የ15 ቀናት ቀጠሮ መሰጠቱ አይዘነጋም።ይሁንና ችሎቱ ከትናንት በስቲያ እሁድ በአራዳ ምድብ ችሎት ሢሰየም ውሳኔውን ያሳለፉት ዳኛ ከቦታው እንዲነሱ እና በቦታቸው ሌላ ዳኛ እንዲተኩ ከመደረጉም ባሻገር፤ ፖሊስ የዛሬ 2 ሳምንት ያቀረበውና በፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተሰጠበት ጥያቄ ዳግም ተነስቶ እና በአዲስ ተተኪው ዳኛ ተቀባይነት አግኝቶ ጦማርያኑ ተጨማሪ የ 28 ቀናት የቀጠሮ ጊዜ ተጠይቆባቸዋል።በዝግ በታየው በእሁዱ ችሎት እንዳለፉ ትጊዜያ ትየታሳሪዎቹ አንዳንድ ቤተሰቦች ወደ ውስጥ እንዲገቡ አልተፈቀደላቸውም፡፡ የጦማርያኑ ቤተሰቦች፣ወዳጅ ዘመዶች፣ጓደኞች እና አድናቂዎች በፍርድ ቤቱ ዙሪያ ተሰብስበው የውሳኔውን ዜና በሚጠባበቁበት ወቅት በስፍራው ተመድበው በነበሩ የስርዓቱ አገልጋይ ጠባቂዎች ወከባ እና መንገላታት እንደደረሰባቸው በስፍራው የተገኘው ሪፖርተራችን ዘግቧል።በተለይም የጦማሪ በፈቃዱ ሀይሉ እናት ጮኸው እስኪያለቅሱ ድረስ በአንዲት ፖሊስ በሀይል እየተገፈተሩ እንዲንገላቱ መደረጋቸው በስፍራው የተገኙትን ሰዎች በሙሉ በእጅጉ ያሳዘነ እና ስሜታቸውን የነካ ሆኗል።

እንዲሁም ችሎቱን እንዳይከታተሉ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ከስፍራው እንዲርቁ በፖሊስ ሲዋከቡ፡ ”ወደፍርድ ቤቱ የመጣነው የፍርዱን ውሳኔ ለመስማትና ወዳጆቻችንን ለማየት ሆኖ ሳለ ለምንእንወጣለን?” የሚል ጥያቄ ያቀረበው ጋዜጠኛ በላይ ማናየ፤ ለሰአታት በፖሊሶች ታግቶ እና መታወቂያውን ተነጥቆ በዛሬው እለት ማእከላዊ ወንጀል ምርመራ እንዲቀርብ ታዟል።ሆኖም ጋዜጠኛ በላይ ዛሬ ወደ ማእከላዊ ቀርቦ መታወቂያውን እንዲመልሱለት ቢጠይቅም፤ መታወቂያውን ሊያገኝ ቀርቶ በወጉ የሚያናግረው አጥቶ ተመልሷል። ጋዜጠኛ በላይ በታገተበት ወቅት በስርአቱ ታማኝ ታጣቂዎች ከደረሰበት ውክቢያ በላይ እጅግ የተሰማው የሰነዘሩበት ስድብ መሆኑን ጠቅሷል። ምን ብለው ነው የሰደቡህ? በማለት ከኢሳት ጥያቄ የቀረበለት ጋዜጠኛ በላይ ማናየ፡-” ስድቡ እኔ ላይ ሳይሆን ህብረተሰቡ ላይ ያነጣጠረ ነው። ብገልጸው በአብሮና ተከባብሮ መኖራችን ላይ መሻከርን ሊፈጥር ስለሚችል እና እንደነሱ መውረድ ስለሚሆንብኝ አልናገረውም” ብሏል።

## ሕዝቡ ለህዳሴዉን ግድብ በነፃ ገንዘቡን ማዋጣት ፈልጎ ነበር

**- ኃ/ማሪያም ደሳለኝ**

የወያኔዩ ሎሌ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በቅርቡ አዲስ አበባ ዉስጥ ዘ አፍሪካ ሪፖርት ከተበላ መጽሄት ጋር ባደረገዉ ቃለምልልስ የኢትዮጵያ ህዝብ ህዳሴዉን ግድብ ለመስራት በነጻ ገንዝብ ለማዋጣት መንግስትን ጠይቆ ነበር ሆኖም መንግስት ይህንን አጋጣሚ ህዝቡ አገራዊ ቁጣባን ማማር እንዳለበት ለማሳሳብና ለማስተማር በነጻ ለምንግሰት ገንዘቡን ከሚሰጥ ቦንድ እንዲገዛ አድርገነዋል በማለት ጠያቂዉን ጭምር ያሳቀ መልስ ሰጥቷል። በዚሁ ቃለ መጠይቅ ወቅት ኃ/ማሪያም የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓታችን 70 በመቶውን ተማሪ የሚያስመር በኢንጂነሪንግና በሳይንስ ነዉ፣ ይኼ ማለት ደግሞ 70 በመቶው ተመራቂ በኢንዱስትሪ ሽግግር ሒደቱ ላይ ይሳተፋል ማለት ነው ብሏል። የኢትዮጵያ የትምህርት ስርዐት ጥራት ከሁለተኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ ድረስ ቁልቁል በወረደበት በአሁኑ ወቅት የአዲስ አበባም ሆነ የሌሎቹ በግማሽ ቀን ተሰርተዉ የተጠናቀቁት ኮሌጆችን ዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች እንኳን እንዱስትሪ መገንባት የተሰጣቸዉን መመሪያ እንኳን በሚገባ ተረድተዉ ለሚቀጥለዉ አካል ማስተላለፍ የማይችሉ እንደገና መማር ያለባቸዉ መሆኑን ብዙ ጥናታዊ መረጃዎች አሳይተዉናል። ሆኖም የዋሁ ኃ/ማሪያም ዩኒቨርሲቲዎችን የሚመለከተዉ እሱ ይማር በነበረባቸዉ ግዜ መነጽር በመሆኑ እንዲህ አይነት ስህተት ዉስጥ ሊዘፈቅ ችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አፍሪካ ሪፖርት የተባለዉ መጽሄት- ኢትዮጵያ ውስጥ የኢንዱስትሪ ሽግግሩን ሒደት የሚያሳልጡት ምንድን ናቸው ብሎ የጠየቀዉን ጥያቄ ሲመልስ ልዩ ጥቅማችንንና ከሌሎች በልጠን የምንገኝባቸውን ሀብቶቻችንን እየተጠቀምን ነው፡፡ በጣም ወጣት የሆነ ሕዝብ ነው ያለን፡፡ መሬት በተትረፈረፈ መጠን አለን። ርካሽ የሆነ የአሌክትሪክ ኃይል አለን፡፡ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን፣ ቅድሚያ ለምንሰጣቸው የኢንዱስትሪ ዘርፎች የተለያዩ ድጋፎችን የምናደርግ ሲሆን፣ ፖሊሲያችንን መሠረት ባደረጉ ባንኮቻችን አማካይነት የገንዘብ ድጋፍ ጭምር እንሰጣለን ብሏል። የዛሬ ሦስት አመት ህንድ አገር ሄዶ ለአንድ የህንድ ቴሌቪዥን ስፍር ቁጥር የሌለዉ መሬት አለን ያለዉ ኃ/ማሪያም አሁንም እንደገና ኢትዮጵያ የተትረፈረፈ መሬት እንዳላት ተናግሯል። የመሬት ይዞታ ጥያቄ አሁንም ባልተፈታበትና ዜጎች ከመሬታቸዉ በሚፈናቀሉበትና መንግስት አንዱን ብሄረሰብ የሰፈርከዉ በሌሎች መሬት ላይ ነዉና ዉጣ እያለ በሚያስገድድበት አገር ዉስጥ ኃ/ማሪያም የተትረፈረፈ መሬት አለን ማለቱ ብዙዎችን ማሰገረም ሳይሆን ያሳቀ ጉዳይ ሆኗል።

## ወያኔ ሀረርና ባህርዳርን በእስርና እንግልት እያመሳቸዉ ነዉ

ሰላማዊ ዜጎችን ከማሰር፤ መበደብደብና ከመግደል ዉጭ ሌላ ስራ የሌለዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ከሰሞኑ ባህርዳርና ሀረር ከተሞች ዉስጥ የሚገኙ ወጣቶችን ከሚማሩበት ት/ቤት ግቢና ከተለያዩ ቦታዎች እየሰበሰበ በማሰር ላይ መሆኑን ምስራቅና ሰሜን ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዜና ዘገባዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። ሀረር ዉስጥ የአቦከር መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ፈተናቸዉን ካጠናቀቁ በኋላ ከግቢያቸው በመውጣት መፈክሮችን እያሰሙ ወደ ማሃል ከተማ በመጓዝ ላይ እያሉ የክልሉና የፌደራል ፖሊሶች ተከታትለዉ በመምጣት ተማሪዎቹን አስረዉ ወደ ፒሊስ ጣቢያ ለምርመራ ወስደዋቸዋል። ተማሪዎቹ ካሰሟቸዉ ዋና ዋና መፈክሮች ዉስጥ “በሀረር ክልል የሚታየው አድሎ ይቁም፣ ፍትሃዊ አስተዳደር ይኑር፣ መንግስት በህዝብ ላይ የሚያደርሰው በደል ይቁም” የሚሉ ይኙበታል። ሌሎችንም መፈክሮች እያሰሙ ተቃውሞአቸውን ሲገልጹ አርፍደዋል።

ፖሊሶች ተቃውሞውን አስነስተዋል ያሉዋቸውን ከ25 በላይ ተማሪዎች እየደበደቡ ወደ እስር ቤት የወሰዷቸዉ ሲሆን የፖሊስን ዱላ ለመሸሽ በሚል በሃረር መካነ-ስላሴ ካቴደራል ቤተክርስቲያን የገቡትን ተማሪዎች አስወጥተው መውሰዳቸውን በተለይ ያሬድ የሚባል ተማሪ በድብደባው ክፉኛ እንደተጎዳ ወኪላችን ገልጿል።የሀረሪ ክልል ባለስልጣናት የሚፈጽሙት አስተዳደራዊ በደል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ነዋሪዎች ይናገራሉ። የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች በሚኖሩባት ሃረር ፍትሃዊ የሆነ ውክልና እንደሌለና የመስተዳደሩ ባለስልጣናት ሁሉንም ብሄሮች እኩል እንደማያስተናግዱ የከተማዋ ነዋሪዎች በምሬት ይገልጻሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ይሄዉ ዘረኛ አገዛዝ ባህርዳር ዉስጥ 27 ተማሪዎችን አስሮ በማንገላታት ላይ አንደሆነ ከባሀርዳር የደረሰን ዜና ያስረዳል። በከተማዋ አውቶቡስ መናሃሪያ ውስጥ ይሰሩ የነበሩ 27 ወጣቶች ጣቢያ 2 ወደ ሚባለው እስር ቤት ተወስደው መታሰራቸውን የአይን እማኞች ገልጸዋል።ከታሰሩት መካከል 9ኙ በማግስቱ ሲፈቱ ቀሪዎቹ አሁንም በእስር ላይ ናቸው። ከተፈቱት መካከል አንዳንዶቹ ያለምንም ምክንያት ወይም የፖሊስ ምርመራ ታስረው እንደተለቀቁ ተናግረዋል።

## በወያኔ መሪዎች ትዕዛዝ በየቦታዉ የሚረሸኑ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በትግራይ ክልል እየተቀሰቀሰ ባለው የህዝብ ቁጣ እንዳስከተለው እየተነገረ ባለው እርምጃም በተምቤን ዓብይ ዓዲ ከተማ በርካታ የህወሓት ካድሬዎች ተገድለው መገኘታቸው ታውቋል።

በተያያዘ ዜና የኦሮሞን ሕዝብ ነጻነት እና የመብት እኩልነት ጥያቄዎችን የሚያነሱና ለፋሽስቱ ሕወሃት አገዛዝ አስጊ ናቸው፤ ሕዝብን ይቀሰቅሳሉ ተብለው የተጠረጠሩ በርካታ ዜጎች ከየመንገዱ እና ጎረቤት አገሮች ጭምር ታፍነው በትግራይ ክልል ውስጥ በሚገኝ እስር ቤት ስቃይ እየተፈፀመባቸው መሆኑ ታውቋል። ቁጥራቸው ከ14 በላይ የሚሆኑ ታሳሪዎች የደረሱበት ባለመታወቁ፤ ምናልባትም በነፈሰ በላው ህወሓት ትዕዛዝ ተረሽነው ይሆናል በሚል ጥርጣሬ ነገሩ ተደፋፍኖ የነበረ ቢሆንም ንፁሃን ዜጎቹ በሕወሓት አገዛዝ ጨለማ ክፍል ታስረው ከፍተኛ ስቃይ እየደረሰባቸው እንደሚገኝ ታውቋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## እየራበንም ቢሆን በምግብ እራሳችንን ችለናል

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

የሚነግረን በጎን ከአለም ባንክና ከለጋሽ አገሮች ጋር የምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልገዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዕርዳታዉ የሚገኝበትን መንገድ እየተደራደረ ነዉ። በምግብ እራሱን የቻለ አገር የአንድ አመት ዝናብ ስለተጓጎለ ብቻ ጓዙን ጠቅልሎ ዕርዳታ ልመና የለጋሽ አገሮችን በር ኣያንኳኳም።

ለመሆኑ ለምንድነዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በእጁ የልመና ስልቻዉን ይዞ በአፉ በምግብ እራሳችንን ችለናል እያለ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚደልለዉ? ኢትዮጵያ በወያኔ ዘመን በምግብ እራሷን ቻለች ብሎ ወያኔን ለመካብና የወያኔን መልካምነት ለመናገር አስቦ ከሆነ ተሳስቷል። ወያኔ የአገራችንን መሬት በቁጥጥሩ ስር አድርጎ እህል አምራቹን ገበሬ ከመሬቱ እያባረረና መሬቱን ለባዕዳን እየቸበቸበ ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን የምትችልበት ሁኔታ ሊፈጠር አይችልም። ደግሞም በምግብ እራሳችንን የምንችለዉ ወያኔ አምርቶ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ አምርቶ ነዉ። የአገራችን የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና የሚረጋገጠዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በምግብ ምርት እራሳችንን ችለናል ብሎ ስለተናገረ ሳይሆን የምግብ ዋስትናችን የሚረጋገጠዉ ወያኔ የኢትዮጵያን ገበሬ የመሬት ባለቤትነት መብትና የኤኮኖሚ ነጻነት ሙሉ ለሙሉ ሲያከብር ብቻ ነዉ። ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ መሬት በግል ይዞታ ስር የሚሆነዉ በኢህአዴግ መቃብር ላይ ነዉ ብሎ በገዛ አፉ እንደተናገረ ኢትየጵያ በምግብ እራሷን የምትችለዉ ኢህአዴግ ሞቶ ሲቀበር ብቻ ነዉ።

ኢትዮጵያ የአገር ሀላፊነት የሚሰማዉና ህዝብ ወድዶ የሚረጠዉ መንግስት ሲኖር በምግብ እራሷን መቻል ብቻ ሳይሆን ታላቅ ፤ ኃያልና ጎረቤቶቿን የምታከብር ጎረቤቷቿም የሚያከብሯት አገር ትሆናለች፤ ያኔ በምግብ እራሳችንን መቻላችንና ታላቅ አገር መሆናችን እኛ ወይም የእኛ መሪዎች የሚናገሩት ሳይሆን ሌሎች ሳይወዱ በግድ የሚናገሩት ሀቅ ይሆናል። እንዲህ አይነቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት የናፈቀዉ ግዜና ዘመን እንዳዉ ስለተመኘነዉ ብቻ ከተፍ አይልም። እንዲህ አይነቱ ሰላም፤ ዕድገት፤ ነጻነት፤ እኩልነትና ፍትህ  የሰፈነበት ዘመን እዉን ለማድረግ ወያኔን ማስወገድና ዘረኛ ስርዐቱን መቅበር  የግድ ይላል። የወያኔ መወገድ ደግሞ የአንዳንዳችንን የህይወት፤ የአንዳንዳችንን የገንዘብ፤ የአንዳንዳችንን የግዜና የግዜና የእዉቀት፤ የአንዳንዳችንን ደግሞ ሁሉን አቀፍ መስዋዕትነት ይጠይቃል። ስለዚህ የዚህ እያንዳንዳችን የዚህ ትግል ጥሪ ቤታችንን ሲያንኳኳ አቤት ብለን ለእናት ኢትዮጵያ ለመድረስ በተጠንቀቅ እንቁም።

## ህወሓት በዉኃ ስም ለጅቡቲ መሬት ቆርሶ ለመስጠት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በመረጋገጡ አካባቢው ተከልሎ የውሃ ሃብቱን እንዲጠቀሙበት ለጅቡቲ መንግስት ለ30 ዓመታት በሚፀና ውል በችሮታ መሰጠቱን ይግለጽ እንጂ የፋሽስቱ ወያኔ ቡድን እያደረገ ያለው ይህ ህገወጥ ሰፊ የድንበር መሬት ችሮታ በመላ አገሪቱ ቁጣን ሊያስነሳ ይችላል በሚል የአገዛዙ ባንዳ ሹማምንት ስጋት ውስጥ መውደቃቸው ከውስጥ ምንጮቻችን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። የመኖሪያ አካባቢያቸው ለጅቡቲ መሰጠቱን ተከትሎ ከአካባቢው የሚፈናቀሉ የሺኒሌ ዞን ነዋሪዎች ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ መወደቃቸው የታወቀ ሲሆን በአካባቢው ነዋሪዎችና በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ መካከል የነገሰው ውጥረት ግጭትን ሊወልድ ይችላል በሚል ስጋት አገዛዙ ቅጥረኛ ሚሊሻዎችን ወደ አካባቢው  ማጓዙ ታውቋል።

ረቂቅ አዋጁን በተመለከተ በጉጅሌው ወያኔ የፓርላማ አባላት ላይ የተደበላለቀ ስሜት የተስተዋለ መሆኑን ያደረሰን የውስጥ ምንጫችን በአማርኛና በእንግሊዝኛ በተፃፉት የረቂቅ አዋጁ ማብራሪያ ሰነዶች ላይ የሃሳብ ልዩነት መኖሩ ከስምምነቱ ጀርባ እየተፈፀመ የሚገኝ አንዳች ደባ ለመኖሩ አመላካች መሆኑም በስፋት እየተነገረ ይገኛል። በአማርኛ የተፃፈው ሰነድ እንደሚያሳየው የጂቡቲ መንግሥት አካባቢውንና ፕሮጀክቱን በባለቤትነት እንደሚያስተዳድር ይግለፅ እንጅ እጅግ በተቃረነ መልኩ በእንግሊዝኛ የተቀመጠው ስምምነት ግን ከእንግዲህ ወዲህ የአካባቢው ባለቤት የጂቡቲ መንግሥት መሆኑን ያውጃል። በጉጅሌው ወያኔ ፓርላማ ብቸኛው የግል ተወካይ የሆኑት ዶ/ር አሸብር ወልደ ጊዮርጊስ ‹‹አዋጁን በጽኑ መቃወማቸው የታወቀ ሲሆን በህወሓት መራሹ ወያኔና በጂቡቲ መካከል የተፈረመው የውኃ አቅርቦት ስምምነት ቢልም፣ ስምምነቱ የመሬት አቅርቦት ነው፤ ለጂቡቲ መሬት እየሰጠን ነው በማለት ፋሽስቱ ወያኔ እያደረገ ያለውን የድንበር መሬት ችሮታ በመቃወም ጉዳዩን የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቀው ዘንድ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ እየተከናዎነ ያለው የአገርን ድንበር በመቁረስ ለባዕዳን አሳልፎ  የመስጠት እኩይ ተግባር በተጠናከረ ሁኔታ መቀጠሉን ተከትሎ በድርጊቱ የታፈነው የህዝብ ቁጣ ፈንድቶ የጉጅሌው ወያኔን አገዛዝ ሊቀብር የሚችል ህዝባዊ አመጽ ሊወልድ እንደሚችል የተጠቆመ ሲሆን በተለይም በቅርቡ ፋሽስቱ ወያኔ ለሱዳን የሰጠውን ሰፊ ለም መሬትን ተከትሎ የተቀሰቀሰው ህዝባዊ ቁጣ ባለመብረዱ የአሁኑ ድርጊት ጉዳዩን ሊያባብሰው እንደሚችልና በቅርቡም ህዝቡ በጋራ የጉጅሌው ወያኔን አገዛዙ ለመቃወም ሊነሳ እንደሚችል ከምንጮቻችን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

## ዘረኛዉ ወያኔ አለም አቀፍ ነጻ ሜዲያዎችን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ማሰራጫ ጣቢያዎችም ተመሳሳይ ችግር እንዳጋጠማቸው ጨምሮ ገልጿል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ዜናዎችንና ሌሎችንም ዝግጅቶች በመቀበል የሚያሰራጨው አረብ ሳት የተባለው ማሰራጫ ተቋም ከማፍያው ሕወሃት ከፍተኛ የሞገድ አፈና እየደረሰበት መሆኑን ጠቅሶ አስፈላጊውን መረጃ በማሰባሰብ ክስ ሊመሰርት መሆኑንም አሳውቃል። ስርጭቱ የሚታፈነው ከኢትኦጵያ በሚመነጭ አፋኝ ጨረር ነው ያለው አረብ ሳት ችግሩን ለመፍታትና ተግባብቶ ለመስራት አልተቻለም፤ የብዙ ደንበኞቻችን ስራም እየተደናቀፈ ነው ስለሆነም አስፈላጊውን ሁሉ በማድረግ ህወሃትንና ገዥዎቹን በህግ እፋረዳቸዋለሁ ሲልም አሳውቋል። ከዚህ በፊት የተለያዩ የተቃዋሚ የራዲዮ ስርጭቶችንና አንዳንድ የቴሌቪዥን ማሰራጫወችን እንዲሁም በኢንተርኔት የሚሰራጩ ዝግጅቶችን ከማፈኑም በላይ እንደ ቪኦኤ ዶቼ ቬሌና ሌሎችንም ስርጭቶች በማወክ ተግባር ተመሳሳይ ውግዘት ሲደርስበት እንደነበርም አይዘነጋም።